# ምዕራፍ ስድስት

# ግጥም

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ የግጥም ዓይነቶችን ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ✓ የቀረበላችሁን ግጥም ዋና መልዕክት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ የዘይቤ ዓይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- ✓ ስለዘይቤ ዓይነቶች ያገኛችሁትን ቁም ነገር በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ✓ በግጥም ዓይነቶች ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት መርዘምና ማጠር ባህሪይ ያላቸውን ቃላት ለይታችሁ ታሳያላችሁ፡፡
- ✓ ስንኞች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ በበቂ ምዕላድ ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ቃላዊ ግጥሞችን መርጣችሁ ትጽፋላችሁ፤ ታነባላችሁ፡፡
- ✓ ከግስ ስምና ቅፅል ትመሠርታላችሁ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጥም ማለት ምን ማለት ነው?
2. የግጥምን ባህሪዎች ታውቃላችሁ? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. ግጥም የሚነበብበት ስልት ከስድ ጽሑፍ የተለየ ነው? ተወያዩበት፡፡

## ግጥም

ስለ ግጥም ምንነት በርካታ ምሁራን የተለያየ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለው የሚነገርለት የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ የሰው ልጆች ለብዙ ዘመናት የአኗኗር ሁኔታቸውንና ልዩ ልዩ ገጠመኞቻቸውን በማንጎራጎርና በማዜም ሐሳባቸውን በጽሑፍ ከመግለጻቸው በፊት በስነ-ቃል መልክ ይጠቀሙበት እንደነበር በስፋት ይነገራል፡፡ በዚህም መሠረት ግጥም ዕድሜው ከቋንቋ መፈጠር ዕድሜ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይገመታል፡፡

ይህ የስነ-ጽሑፍ ዘርፍ ዕድሜው ረጅም በመሆኑ እንደየዘመኑ ፍልስፍና፣ ገናን የኪነጥበብ ፈለግ፣ እንደየገጣሚውና እንደየስነጽሑፍ አዋቂው አተያይና የኪነጥበብ ዝንባሌ የተለያዩ ብያኔዎች ሲሰጡት ቆይተዋል፤ ከዚህም የተነሳ ሁሉንአቀፍ የሆነ አንድ ወጥ ብያኔ ይህ ነው ብሎ መቀበል ቀላል አይሆንም፡፡

ግጥም አንድን ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ የማሳየት ሀሳብን አክርሮና አግዝፎ የማቅረብ ችሎታ ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና በሙዚቃዊ ቃናው የስሜት ህዋሳትን በቶሎ የሚነካ፤ ለስሜት ቅርብነት ያለው ኪነጥበብ ነው፡፡ የግጥም ባህሪያትን ስንመለከት የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

አንደኛ፣ ግጥም በእጅጉ **ቁጥብና እምቅ** ነው፡፡ በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት የሚችል የስነጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ግጥም **ምጣኔ** ያለው ነው፡፡ በግጥም ውስጥ የቀለማትን መጠን በሐረግ ውስጥ የምንመጥንበት /የምንለካበት/ ዘዬ ምጣኔ ይባላል፡፡

ከዚህም ሁኔታ እንደምንረዳው ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በሐረግ ውስጥ ሲሆን መለኪያው ደግሞ ቀለም መሆኑን ነው፡፡ ታዲያ "ቀለም ማለት ምንድነው?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ቀለም ማለት፡-

ሀ. ተናባቢና አናባቢ ድምጾች አንድ ላይ ሲመጡ የሚፈጥሩት የቋንቋ መዋቅር ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** "ና" የሚለው በድምጻዊ አጻጻፍ ሲጻፍ /ንኣ/ የሚሉትን ድምጾች ይወክላል፡፡

ለ. አናባቢ ድምጽ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** እ /ኧ/ ኧ /ኧ/ ኡ /ኡ/...

ይህን ከተረዳን የግጥም ሐረግ እንዴት በቀለም እንደሚመጠን ደግሞ እንመልከት፡፡

**ምሳሌ፡-** አንበሳ ነው ጀግና ቁጣው አስበርጋጊ፣ ፮ + ፮ = ፲፪

የነፃነት አርማ የድል ፋና ወጊ፡፡ ፮ + ፮ = ፲፪

በዚህ መሠረት በየሐረጉ ስድስት፣ስድስት ቀለም መኖሩን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡ በሐረግ ስድስት ቀለሞችን የሚይዝ ግጥም የወል ሐረግ /ግጥም/ ተብሎ ይጠራል፡፡ ሲጠቃለል ሐረግ ማለት የመጀመሪያዋን ድምጽ ማሰማት ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ **ከፊል እረፍት እስከ ምናደርግበት** ጊዜ ድረስ ያሉ የቀለማት ስብስብ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ፣ **ግጥም ምት** አለው፡፡ ምቱ የሚመነጨውም ከምጣኔው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንዳየነው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን የማለቱ ሁኔታ ነው ምቱን የሚፈጥረው፡፡ ይህን ለመረዳት አንድ አባት የስድስት ዓመት ህፃን ልጁን ይዞ ወደ ሱቅ ሲራመድ ያለውን የሁለቱን ርምጃ ልዩነት ማስተዋል ይበጃል፡፡

የአባት ርምጃ ሰፋ ሰፋ ያለ፤ የልጁ ደግሞ ጠበብ ጠበብ ያለ በመሆኑ ምታቸው አንድ አይሆንም፡፡ ከዚሁ አንጻር ሐረግ በሚይዘው የቀለም ብዛት መጠን ምቱ ይለያያል፤ ዓይነቱም እንዲሁ፡፡

**ምሳሌ:-** "ቡሄ በሉ" የምንልበት ጊዜና "ካላጨበጨቡ" የምንልበት ጊዜ ይለያያል። ምክንያቱም የመጀመሪያው ሐረግ አራት ሁለተኛው ስድስት ቀለም በመያዛቸው የተነሳ ነው። ብሉ ህሌ ብሽ ልሉ = ፬ ቀለሞች
ክኣ-ልኣ-ጭኻ-ብሽ-ጭኽ-ብሽ=፮ ቀለም

አራተኛ፣ **ግጥም ዜማ** አለው። ይህ የሚፈጠረው የተስተካከለና የተከረከመ ምጣኔና ምት በሐረጉ ውስጥ በመኖሩ የተነሳ ነው። ምጣኔ ከተዛባ ምቱ፣ ምቱ ከተዛባ ደግሞ ዜማው የተዛባ ይሆናል ማለት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለጸው የግጥም ዓይነቶች የሚወሰኑት በሐረግ ውስጥ በሚኖሩ የቃላት ብዛት ነው። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ተመልከቱ።

- **የወል ግጥም:-** በሐረጉ ውስጥ ስድስት ቀለማትን የሚይዝ የግጥም ዓይነት ነው።

**ምሳሌ:-** አንቺ ልጅ አንቺ ልጅ / የጎረቤታችን፤ ፮ + ፮ = ፲፪
እናትሽ ተቆጡ / አትምጪ ቤታችን። ፮ + ፮ = ፲፪

- **ሰንጎ መገን ግጥም:-** በሐረጉ ውስጥ አምስት ቀለሞችን አካቶ የሚይዝ ግጥም ነው።

**ምሳሌ:-** ፈረ ጨነቀው / ተርበደበደ፤ ፭ + ፭ = ፲
ጥይት ዘነበ / እሳት ወረደ። ፭ + ፭ = ፲

- **ቡሄ በሉ/ የህፃናት /ሆያሆዬ/ ግጥም:-** በየሀረጉ ከአንድ - አራት ቀለማትን የሚይዝ የግጥም ዓይነት ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በአቀንቃኝና በተቀባይ መካከል በአብዛኛው በቅብብሎሽ ስለሚከወን ነው።

**ምሳሌ:-** አቀንቃኙ:- " ሆያ ሆዬ" ሲል:-
ተቀባይ "ሆ" ወይም "ሆዬ" ይላል። ይኸውም "ሆያ ሆዬ" በሚለው አራት ቀለማት፣ "ሆ" በሚለው ደግሞ አንድ ቀለም፣ እንዲሁም "ሆዬ" በሚለው ውስጥ ደግሞ ሁለት ቀለማት ይገኛሉ። ስለዚህ ከአንድ እስከ አራት ቀለማት በሐረጉ ውስጥ ይከሰታል ማለት ነው።

© MoE, FDRE Not to be republished

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ቀጥለው የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. የግጥምን ዕድሜ በትክክል ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር ይቻላል::
2. ግጥም ለደስታ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ስሜቶችም መግለጫ ነው::
3. ስድ /ዝርው/ ጽሑፍ እና ግጥም ስሜትን ለማስተላለፍ እኩል ናቸው::
4. ቀለም ማለት ተናባቢ ድምጽ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው መዋቅር ማለት ነው::
5. ምት ማለት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን መጥራት ማለት ነው::

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

1. የግጥም ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ቁጥብ አይደለም ሐ. ዜማ አለው
   ለ. ምት አለው መ. ምጣኔ አለው
2. ቁጥብነት ሲባል የ______ ቁጥብነት ማለት ነው::
   ሀ. የሐሳብ ሐ. የቃላት
   ለ. የጽንስ ሐሳብ መ. ሁሉም
3. የሰንኙ መገን ግጥም በሐረግ ስንት ቀለም አለው?
   ሀ. ፬ ለ. ፫ ሐ. ፮ መ. ፯
4. ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በ _____ውስጥ ነው
   ሀ. ስንኝ ሐ. ሐረግ
   ለ. ቀለም መ. ቤት
5. ለአዕምሮ የሚጥም ባለ ስልት የቋንቋ አደራደር ______ ይባላል::
   ሀ. ስነ ግጥም ሐ. ሐረግ
   ለ. ስንኝ መ. ቀለም



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced



## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. በምዕራፍ አራት ስለ "ቅስቀሳና ማነቃቂያ ንግግር" በተማራችሁት መሠረት ለቅስቀሳ አላማ የሚሆኑ ግጥሞችን ከተለያዩ መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች በመውሰድ ክፍል ውስጥ አቅርቡ።
፪. ከመጻሕፍት ከጋዜጣ ከመጽሔቶች...ያገኛችሁትን ግጥም በሚገባ አንብባችሁ ዋናውን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ግለጹ።
፫. መምህራችሁ በቡድን ከከፈሏችሁ በኋላ በየቡድናችሁ በመሆን ከዚህ በሚከተሉት በአንዱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ቃላዊ ግጥሞችን አሰባስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሀ. የልመና ቃላዊ ግጥሞች
ለ. የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች
ሐ. በክብረ በዓል ላይ የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞች
መ. በለቅሶ ላይ የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞች/ሙሾ/
ሠ. ሌሎች በእናንተ አካባቢ የሚነገሩ የሥራ ቃላዊ ግጥሞች፡- ለምሳሌ የመኸር፤ የመዝሪያ፣ የማረሻ ጊዜያትን የተመለከቱ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

## ክፍል ሶስት፣ ሰዋስው

፩. ቀጥለው በተሰጡት ምሳሌዎች መሠረት ቅጥያ ምዕላዶችን በበቂ ምዕላዶች ላይ እየጨመራችሁ አገልግሎታቸውን አብራሩ።

| | ነፃ ምዕላድ | + ጥገኛ ምዕላድ | = ቃል | የቅጥያ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | እህት | - ህ | = እህትህ | የአንተ እህት (ባለገንዘብነትን አመልካች) |
| 2. | | | = ሳምሽ | |
| 3. | | | = ወንድሙ | |
| 4. | | | = አባቷ | |
| 5. | | | = ወሬዎች | |
| 6. | | | = ስንቂ | |

**፪. ቀጥለው በቃል ደረጃ የተሰጡትን ምዕላዶች ነፃ ምዕላድ ጥገኛ ምዕላድ በማለት ከፋፍሉ:: የጥገኛ ምዕላዶቹን አገልግሎትም ግለጹ::**

| | ቃል | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መርከበኛ | መርከብ | -ኧኛ | ቅጽል መስሪች |
| 2. | ሆዳም | | | |
| 3. | ወተታም | | | |
| 4. | ተራራማ | | | |
| 5. | ጎጠኛ | | | |
| 6. | ቂልነት | | | |

## በቃላት ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች

በአማርኛ የቃላት ሥርዐት ውስጥ አንዳንድ ድምጾች በቃላት ውስጥ ሲጠብቁና ሲላሉ የትርጉም ለውጥ ያሳያሉ:: ይሁን እንጂ፣ በማንኛውም ቃል ውስጥ የሚገኙ ድምጾች በመጥበቅና በመላላት የተለያዩ ትርጉም ይሰጣሉ ማለት ግን አይደለም:: የትርጉም ለውጥ ያስከትላሉ የተባሉትን በተለያዩ ዐውዶች አስገብቶ ማየትም ለግንዛቤ ይጠቅማል::

**ምሳሌ:-** አበበ ሰባ ብር ሰጠኝ:: → (ላልቶ ሲነበብ) በቁጥር ፸ ብር
የአየለ በሬ ሰባ:: → (ጠብቆ ሲነበብ) ሰውነቱ ስብ አከማቸ፣ (ጮማ ሆነ)

**፫. በምሳሌው መሠረት በግጥሙ ውስጥ ካሉ ቃላት ውስጥ ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ልዩነት የሚያመጡ ቃላት ለዩ::**

ሆ ይላል ገበሬ፣
ዲብ እያፈረሰ ባሽልማ በሬ፣
በርዬ በርዬ
አንተን የቻለ ሰው፣
ቶሎ ቶሎ ብለህ፣
አንጀቴን አርሰው፣
እረኛህ ያለቅሳል
ምሳው እያነሰው::

*(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነፅሑፍ መሠረታውያን፣ በምሳሌነት ከተጠቀሙት፣ (47)::)*

© MoE, FDR
Not to be rep

## በቃላት ውስጥ የሚርዝሙና የሚያጥሩ ድምጾች

ይህ ፅንሰ ሐሳብ ከፍ ሲል ካልነው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጠብቆ ተነበበ ማለት ተረግጦ ተነበበ ማለት ነው፡፡ ተረግጦ ተነበበ ማለት ደግሞ ድምጽ ረዝሞ ተነበበ ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** ሀ. ገና /ግእንኣ/ ስወደፊቱ ማለት ነው፡፡ (ላልቶ)

ለ. ገና /ግእንንኣ/ ማለት ደግሞ የገና በዓል ማለት ነው፡፡ (ጠብቆ)

ከዚህ የምንረዳው "ገና" በሚለው ውስጥ ተነባቢ ድምጽ /ን/ ተደግሞ እንደተጻፈ ልብ ይሏል፡፡ ሌላው ሳድስ ድምጾች ቀለም የሚሆኑበትም የማይሆኑበትም ጊዜ አለ፡ ይኸውም በቃል መጀመሪያ ላይ ተጽፈው ከተገኙ ሁልጊዜ ቀለም ይሆናሉ፡፡

**ምሣሌ፡-** ፍቅር /ፍእቅር/ በሚለው ውስጥ /ፍ/ ከሚለው ድምፅ ቀጥሎ /እ/ የምትባለዋ አናባቢ ድምጽ ስለመጣች /ፍእ/ ቀለም ሆኗል፡፡ ሌሎች /ቅ/ ና /ር/ ግን ቀለሞች አይደሉም፡፡

በሌላ በኩል ሳድስ ድምጽ በቃል መጨረሻ ሆኖ የሐረግ መጨረሻ ከሆነና ተረግጦ ከተነበበ ቀለም ይሆናል፡፡

**ምሳሌ፡-** በድንገት ተያይተን /ፍቅር ቢይዛት ፮–፮ ቀለሞች
እኔም ተሸነፍኩኝ /ልቤን ሰጠኋት ፮–፮ ቀለሞች

**አስተውሉ፡-** በዚህ ግጥም ውስጥ በሁለቱም ስንኞች የመነሻ ሐረጎቹ ማለቂያ ሆሄያት ሳድሶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ቀለማት አይደሉም፡፡ ባንፃሩ የሁለቱም ስንኞች መድረሻ ሐረጎች መጨረሻቸው ሳድስ ሲሆኑ ቀለማት ሆነዋል፡፡ ሲጻፉም /ብኢይዝኣትትእ/ እና /ስእጥእህኡኣትትእ/ ነው፡፡ ስለዚህ ረዝመው ተነበው ቀለም ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ድምጾች ተጎርደው የሚቀሩበት መንገድም አለ፡፡

**ምሳሌ፡-** እጅግ ያቀናል መንገዱ፤
እዳር ተቀምጦ ላየው፤
<u>ማዕበል</u> ይጎዳል ሰው፡፡

የተሰመረበት ቃል ሲያጥር /ዕ/ ቀለም አይደለችም፡፡ በመሆኑም "ማበል" ወደሚል ቃል ትርጓሜው ይቀየራል፡፡ ስለሆነም ያሉት ቀለማት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**፬. ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ውስጥ በማስረዘም የተጻፉትንና ያጠሩትን ለይታችሁ በማውጣት የተከሰተውን የትርጉም ልዩነትም ሆነ የተከናወነውን የቀለም ምጣኔ አስረዱ፡፡**

**ግጥም 1፡-**

በበቅሎ ሆኜ ስዞር፤
ካንዱ ወደ አንዱ አገር፤
በህልሜም አይደል በእውኔ፤
ብዙ ጥብቅ አየሁ እኔ፡፡

**ግጥም 2፡-**

ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ሰለሞን፤
እጠይቀው ነበር በተገናኘን፤
ሞት እሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?

**፭. ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡት ቃላትና ሐረጋት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለተለያዩ ተግባራት መለማመጃነት በቀረቡላችሁ ግጥሞች ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ አገባባዊ /አውዳዊ/ ፍቻቸውን ለክፍል አቅርቡ፡፡**

1. ዐዋይ
2. ጨፌ
3. ባድማ
4. ይፋ
5. አደባባይ
6. አንጀቱን አርሰው
7. ትቢያ

**፮. ቀደም ሲል ከቀረቡት ግጥሞች ውስጥ ለወጡት ቀጣዮቹ ስንኞች በራሳችሁ አባባል ትርጓሜ ስጧቸው፡፡**

1. ሰላም ሲልሽ ቆሟል ከደጅሽ ፍጥረቱ ____________________
2. ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ______________________
3. ከስም አደባባይ __________________________________

4. ሞት እሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን_______________

5. ህይወቱን ኮነንሽው_______________

፯. በምዕራፍ አራት ከግስ ስምና ቅጽል እንደሚመሰረት ተምረናል፡፡ በመቀጠል፡-

ሀ. ከቀረቡት ግሶች ስምን መስርቱ፡፡

**ምሳሌ፡-**

| ጥገኛ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ | ስም |
|---|---|---|
| ውፍር | -ኧት | ውፍረት |
| ድፍር | -ኧት | ድፍረት |
| ድርስ | -ኧት | ድርሰት |
| 1. ውልድ | ? | ? |
| 2. ክስር | ? | ? |
| 3. ቅርብ | ? | ? |
| 4. ግሽብ | ? | ? |

ለ. ከቀረቡት ግሶች ቅጽሎችን መስርቱ፡፡

| ምሳሌ፡ | ግስ | ውልድ ቅፅል |
|---|---|---|
| | አጠረ | አጭር |
| | ወፈረ | ወፍራም |
| | ከበረ | ክቡር |
| 1. | ዘረፈ | ? |
| 2. | በላ | ? |
| 3. | ከሳ | ? |
| 4. | ሰከረ | ? |

፰. በሚከተሉት ባዶ ቦታዎች ላይ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡትን ግሶች ወደ ቅፅል እየቀየራችሁ ሙሉ፡፡

1. ከገበታው ላይ አንድ_______ (ቆረጠ) ዳቦ ወሰድሁ፡፡
2. ከትናንት ወዲያ አንድ_________ (ተለቀ) ሰው ወደ ቤቴ መጥቶ ነበር፡፡



© MoE, FDRE, Ethiopia Not to be reproduced

3. እንደእርሱ ያለ __________ (ታተረ) ሠራተኛ አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡
4. ሊሸጣት ወደዝያ የወሰዳትን __________ (ከሳ) ላም የሚገዛው አላገኘም፡፡
5. እንጀራ በ ______________ (ጠበሰ) ስጋ በላሁ፡፡
6. ሙስና ሀገርንና ወገንን___________ (ገደለ) በሽታ ነው፡፡

## ክፍል አራት፣ ስነ-ጽሑፍ

፩. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ግጥሞች በማዳመጥ ቀደም ሲል በተማራችሁት መሠረት የግጥም ዓይነቶቹን ‘የወል’፣ ‘የሰንገ መገን’ ወይም ‘የቡሄ በሉ’ ግጥም በማለት መልስ ስጡ፡፡

፪. ሀ. ስለትምህርት ቤታችሁ ንጽህና ሁኔታ ባለ ስድስት ስንኝ ግጥም ገጥማችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
ለ. በፋከራ ወቅት የሚፎከርበትን የሰንጎ መገን ግጥም ስልት በመጠቀም ባለ አራት ስንኝ ግጥም ገጥማችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡
ሐ. በአካባቢያችሁ ልጆች በዜማና በግጥም የሚሳተፉበት ጨዋታ ካለ ግጥሙን ጽፋችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

፫. ስለዘይቤ ባለፈው ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ቁም ነገሮች በማስታወስ ቀጥለው በተሰጡት ግጥሞች ውስጥ፦

ሀ. ከዘይቤ ዓይነቶቹ ውስጥ የትኛውን /እንቶኔ፤ምፀት ወይስ ግነት/ እንደተጠቀምን ግለጹ፡፡
ለ. ዘይቤዎቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት በአጭሩ ጽፋችሁ አስረዱ፡፡

**ግጥም 1.**

ብቅ በይ-
ብቅ በይ ጣይቱ፣
ወጣ በይ-
ወጣ በይ ውቢቱ-
ሰላም ሊልሽ ቆሟል ከደጅሽ ፍጥረቱ፡፡

*(ደበበ ሰይፉ)*

**ግጥም 2.**

ጽጌያቱ ደረቁ፣ ንቦችሽ አለቁ፣ ሰዎችሽ ደቀቁ፣
ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ፡፡
ዐዋይን ሰማሁዋት ስታለቅስ በይፋ፣
ከጎጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፋ፡፡

*(ደበበ ሰይፉ)*

**ግጥም 3.**

ከፍ በል ወደ ላይ፣
ከስልጣኑ ሰማይ፣
ከስም አደባባይ፡፡
በሀብት ከፍ ከፍ፣
በሹመት ከፍ ከፍ፣
ከፍ ከፍ፣
ከፍ ከፍ፣
ከዚያ የወደቅክ እለት፣
አጥንትህ እንዳይተርፍ፡፡

*(ታገል ሰይፉ)*

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ:-

የግጥም ምንነትና ባህሪያቱን ተመልክተናል:: በዚህም ግጥም ቀጥብና እምቅ እንዲሁም ምትና ዜማ እንዳለው ተመልክተናል:: የወል ግጥም፣ ሰንገ መገን ግጥም እንዲሁም ቡሄ በሉ ግጥምን ባህሪያት አይተናል:: እንቶኔ፣ ምፀት እና ግነት ዘይቤ በግጥም ውስጥ የሚቀርቡበትን መንገድ ተመልክተናል:: የነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ምንነትና ተግባር ተምረናል:: በቃላት ውስጥ የሚጠብቁና የሚላሉ ድምጾች እንዲሁም በቃላት ውስጥ ድምጾች የሚፈጥሩት የፍች ልዩነት ተመልክተናል:: ስንኞች የሚያስተላልፉን መልእክት በራስ አባባል እንዴት መግለጽ እንደሚቻል ተለማምደናል:: የቅስቀሳና የማነቃቂያ ግጥሞችን በመሰብሰብና ክፍል ውስጥ በንግግር በማቅረብ ዓይነታቸውን ለይተናል:: የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን በመመርመር ይዘታቸውን ለይተን ተመልክተናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ግጥም ከስድ ንባብ የሚለይባቸውን ባህሪያት ጥቀሱ::
2. በግጥም ውስጥ ቀለም የምንለው ምንድነው?
3. የሰንገ መገን ግጥም ባለ ስንት ቀለም ግጥም ነው?
4. የወል ግጥም ባለ ስንት ቀለም ግጥም ነው?
5. ጥገኛ ምዕላዶች በነፃ ምዕላዶች ላይ ሲጨመሩ ምን አገልግሎት ይሰጣሉ?
6. ቀጥሎ የቀረበው ግጥም በየትኛው የዘይቤ ዓይነት የቀረበ ነው?

   እንደ ሰው ተወልዶ እንደሰው የማይኖር
   እንደ ሰው የማይሞት እንደሰው ሲቀበር
   አይተሽስ ሰምተሽስ ታውቂያለሽ ወይ ምድር
   ፍረጂኝ! መስክሪኝ!ይህን ክፉ በደል::

*(አበራ ለማ፣ ለኔልሰን ማንዴላ 1977)*

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ግጥም ምንነትና ዓይነቶች ከቀረበው ምንባብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የተለያዩ የግጥም ዓይነቶች እንዳሉ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የአንድን ግጥም መልእክት አገልፃለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የዘይቤ አይነቶችንና አገልግሎት መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | በነፃና ምዕሳዶች የተጨመሩ ቅጥያዎችን ተግባር አገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የቃላት መጥበቅና መላላት የሚያመጣውን የፍች ልዩነት አገልጻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced/published